04/10/99

# የዛሬው ዕለት (ሰኔ 4/1999) የዋለው ችሎት ሂደትና ሕጋዊነት በአጭሩ

## ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም

ግንቦት 24/1999 በዋለው ችሎት የቪድዮና የኦዲዮ ማስረጃዎች ተሟልተው እንዲታዩ ተጨማሪ ቀጠሮ እና በተከሳሾች በኩል፣ ሁሉንም ማስረጃዎች ከተመለከትን በኋላ የመከላከያ ማስረጃ እንድናቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ለዛሬ ተቀጠረ። ከዚህ በተጨማሪ አቃቤ ሕግ የምስክሮች ዝርዝር አስቀድሞ ይድረሰኝ ብሎ በጠየቀው ጥያቄ ላይ ክርክሩ ውስጥ የነበሩት የሲቪክ ማሕበራት ሃላፊዎች ምስክሮች ማስፈራራት እየተደረገባቸው ሊመሰክሩልን አልቻሉም፤ አቃቤ ሕግም የምስክሮች ስም ለተከሳሾች እንዳይሰጥ ተቃውሞ፣ ፍርድ ቤቱም ተቀብሎት፣ ይህ ሥርዐት በእኛ ጉዳይ ቀጥሏል። አሁን በእኛ ጊዜ አቃቤ ሕግ ያላደረገውን ነገር እኛ እንድናደርግ መገደድ የለብንም ብለው ተቃውመው ስለነበር በእዚህ ጉዳዮች ሁሉ ትዕዛዝ ለመስጠት ለዛሬ ተቀጥሯል። እኛ ተከራከሩ ተብለን ትዕዛዝ ሲሰጥብን (ሚያዝያ 1 1999 ማለት ነው) እንከላከላለን ወይም አንከላከልም ብለን ከመወሰናችን በፊት በኢትዮጵያ ሕገመንግስትና የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ኢትዮጵያ ተቀብላ ባፀደቀችው ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች መሠረት እንዲከበሩልን የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርበን ነበር።

1. የአቃቤ ሕግ የቪድዮና የኦዲዮ ማስረጃና ጭብጥ፣
2. ብይኑና የምስክሮች ቃል፣
3. ከቤታችንና ከፅ/ቤታችን የተወሰዱብን ዶክሜንቶች ኮምፒዩተሮች ከነፋይሎቻቸውና ሌሎች ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ የግልና የድርጅቱ ንብረቶች እንዲሰጡን፣
4. ማረሚያ ቤት ከገባንበት ጊዜ አንስቶ በተለያየ ጊዜ የተወሰዱብን የየዕለት የችሎት መከታተያ ማስታወሻዎች፣ አጀንዳዎች፣ ለክርክሩ ያዘጋጀናቸው ጽሑፎች ማስረጃዎች የተለያዩ ሰነዶችና ስራዎች የግል ንብረቶቻችን ስለሆኑ እና ለመከላከልም አስፈላጊ ስለሆኑ እንዲመለሱልን ጠይቀን ነበር።
5. ጉዳያችን ያድማ ወንጀል ነው ስለዚህ በአንዱ ላይ የቀረበው ሁላችሁንም ይመለከታል ስለተባለ እና የጋራ ሃላፊነታችን አለባችሁ ተብሎ ስለተበየነ

በጋራ ተገናኝተን እንድንወያይና ማስረጃም መሰብሰብ እንድንችል ጠይቀን ነበር።

<u>ማስታወሻ፡</u> እነዚህን ጥያቄዎች መጀመሪያ ያቀረብነው ሚያዝያ 1/1999 ዓ.ም. ተከላከሉ የሚለውን ብይን ሰጥተው እንደጨረሱ ወዲያውኑ በችሎት ፊት ነበር። ዳኞች ግን አሁን አንሰማችሁም ብለውን ጥለውን ወጡ። ወደ ማረሚያ ቤቱ ከተመለስን በኋላ እንደገና በማመልከቻ አዘጋጅተን በማረሚያ ቤቱ በኩል ላክን። ማረሚያ ቤቱ ግን ለፍርድ ቤቱ ያቀረብነውን አቤቱታ የፍርድ ቤቱን ሥልጣን ወስዶ፣ መርምሮ መልስ ሰጠን። መልሱም ማመልከቻ ወይም አቤቱታ ማቅረብ የምትችሎት በግል እንጂ በጋራ የአንድ ማመልከቻ ማቅረብ አትችሉም አለን። ይህ መልስ ሁለት መሠረታዊ ስሕተት ነበረው።

አንደኛው ለፍርድ ቤት የሚቀርብን አቤቱታ፣ ማረሚያ ቤቱ መርምሮ የመወሰን ሥልጣን የለውም፤ ተቀበለውም አልተቀበለውም ወሳኙ ፍ/ቤቱ ነው። ማረሚያ ቤቱ በወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዐት መሰረት የእኛን ማመልከቻ ወስዶ ለፍርድ ቤቱ ማድረስ ብቻ ነው የነበረበት። ሁለተኛው በሕገመንግስቱ አንቀፅ 37 መሰረት ምንም በማያሻማ ሁኔታ የተደነገገ መብታችን ነው። ከዚህ በተጨማሪ አቃቤ ሕግ ወንጀሉን የሠሩት በአድማ ስለሆነ የሚቀርበው ጭብጥና ማስረጃ ሁሉንም ይመለከታል ብሎ ፍርድ ቤት ደጋግሞ ተከራክሮለታል። ለአቃቤ ህግ ሲሆን በጋራ ነው የምትከራከሩት ሲሉን የቆዩት ሰዎች ለእኛ ሲሆን አድማ አይሆንም በግላችሁ ካልሆነ አቤቱታ (ከላይ የተቀመጡትን ጥያቄዎች የያዘ) ከእኛ ወስዶ ሲያበቃ ለፍርድ ቤቱ አላደርስም ለእናንተም አልመልስም አለን።

ሚያዝያ 22/1999 በዋለው ችሎት የመከላከያ ማስረጃ መግለጫ ለምን አላቀረባችሁም ብሎ ሰብሳቢው ዳኛ አዲል አህመድ ጠየቀን። ተነስተን ማረሚያ ቤቱ የፈፀመብንን በደል አስረዳንና ጥያቄዎቻችንን ደግመን በቃል ለፍርድ ቤቱ ለሁለተኛ ጊዜ አቀረብን። የፅሑፉን አቤቱታ ማረሚያ ቤቱ እንደወሰደው አስረዳን። ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አጣርቼ ትእዛዝ እሰጣለሁ በማለት ለሚያዝያ 24/99 ተቀጠረ።

ሚያዝያ 24/99 በዋለው ችሎት እኛ ከጠየቅናቸው ጥያቄዎች 3 ዓይነት መልሶች ሰጡ። አንደኛው ሊከበርላችሁ ይገባል ስለዚህ ይሰጣችሁ የሚል (positive) ሁለተኛው

http://mesfinwoldemariam.org

አትችሉም አታገኙም፣ ዝም ብላችሁ ተከላከሉ የሚል (negative) ቃስተኛው ይገባችኋልም አይገባችሁምም ሳይል፣ አውቆ እንዳላወቀ ማለፍ (Tacit denial) ናቸው፡፡

1. ለመከለከል ያስፈልጋችኋል ስለዚህ ይሰጣችሁ የተባልናቸው የብይን ግልባጭ እና የቪድዮና የኦድዮ ማስረጃ ለእናንተም ሆነ ለጠበቆች አይሰጥም፤ በማረሚያ ቤቱ ግን ተከፋፍላችሁ በቡድን እንድታዩት ብቻ ይደረግላችኋል ተባለ፡፡

2. የምስክሮች ቃልን ከቤታችንና ከፅሕፈት ቤታችን የተወሰዱብን ከላይ የተጠቀሱትን በሙሉ አይሰጣችሁም ተባልን፡፡ እነዚህ የተወሰዱብን ንብረቶች የግላችን ከመሆናቸውም ባሻገር ለመከላከል እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው፤ ግን ተከለከልን፡፡

3. ከማረሚያ ቤት የተወዱብን ንብረቶቻችን ፋይሎች፡ ፅሑፎች፣ ሰነዶችና የፍርድ ቤት ውሎ ማስታወሻዎች እና ማስረጃዎች እንደዚሁም የኦድዮ ማስረጃን በተመለከተ አቃቤ ሕጉ ያቀረበውን ጭብጥ በተመለከተ ምንም ሳይሉ አለፏቸው፡፡

ከማረሚያ ቤቱ የተወሰዱብን ለክርክሩ አስፈላጊ የሆኑ ራሳችን ያዘጋጀናቸው ሰነዶችና ማስረጃዎች ናቸው፡፡ የኦድዮና የቪድዮ ማስረጃ ጭብጥን በተመለከተ በዓይናችን ተመልክተን የመከላከያ ማስረጃ የምናዘጋጀው የቀረበውን ጭብጥ ሳንይዝ አቃቤ ሕግ በቪድዮዎች ላይ ምን ምን ወንጀል ተሠርቷል እንዳለ ሳናውቅ ስለሆነ ለመከላከል ያስቸግረናል፡፡ ፍርድ ቤቱ ግን ይህን አውቆ ይሰጣችሁ እንዳይል፣ ክሳችንን በበቂ ሁኔታ ተረድተን መከላከል ልንችል ሆነ፡፡ አይሰጣችሁም እንዳይል ደግሞ የግድ አስፈላጊ ስለሆነ እሺም እምቢም ሳይል አለፈው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የምስክሮች ቃልን ፍርድ ቤቱ በብይን ላይ አንዱንም አልተመለከተውም፤ ዝም ብሎ የአቃቤ ሕግን ጭብጥ ብቻ ተመልክቶ፣ ምስክሮቹ ያንን ጭብጥ እንደመሰከሩት አስመስሎ ተጠቅሞበታል የምስክሮቹ ቃል ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ስለዚህ እኛ ፍ/ቤት እየተከታተልን የመዘገብነውን ሰነድ ቀሙን፤ ከፍርድ ቤት መዝገብ ላይም ተገልብጦ ይሰጠን ስንል አይሆንም አሉን፡፡

ሚያዝያ 24/1999 ይህን ትዕዛዝ ሰጥተው እንደጨረሱ፣ የከለከላችሁንንስ አንዴ አይችሉም ብላችኋል፡፡ ግማሾቹን እኮ እንዳውም አላነሳችኋቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ

http://mesfinwoldemariam.org

የእኛን ጥያቄ ( ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ አላቀርብም ያለውን) ማረሚያ ቤቱን እናጣራለን ብላችሁ ነበር፣ አጣርታችሁ ምን ደረሳችሁ? የእኛን ማመልከቻ ማረሚያ ቤቱ እየመረመረ ትዕዛዝ የሚሰጠን ለምንድን ነው? ምን ሥልጣን አለው? ጥያቄያችንን ለምን ለፍርድ ቤቱ አያቀርብልንም። ለዚህ እና ለሌሎች ላቀረብናቸው 2 ጥያቄዎች ይገባልም አይገባምም ሳትሉ አልፋችሁታልሥ የሚል ጥያቄ ለማንሳት እጃችንን አወጣን:: እንዳንናገር ዕድል ሲነፈገን የተከበረው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይሰጥበት የታለፈ አቤቱታ አለን፣ አሁንም ፍርድ ቤቱ ያዳምጠን አልን:: ቆይ በመጨረሻ ትናገራላችሁ አሉንና ቀጠሮ ለሌላ ጊዜ ሰጥተው መንገድ ጀመሩ፣ አቤቱታ አለን እያልን እያመለከትን እንደቆምን ጥለውን ሄዱ::

- በሚያዝያ 24 እና በሰኔ 4 መካከል መሉነህና አንዱዓለም በሞት አደጋ ላይ ደርሰው ነበር:: በተለይ ሙሉነህ በጣም ደክሞ ስለነበር ሰኔ 4ም ፍርድ ቤት አልቀረበም:: የማረሚያ ቤቱ ተወካይ በውሸት ሙሉነህ አሞኛል ስለአለ ፍርድ ቤት አልቀረበም፤ ለመቅረብ ፈቃደኛ አይደለም አለ:: ይህም ሐሰት መሆኑን፣ እውነቱ ማረሚያ ቤቱ ከፈፀመበት ግፍ በሞት አደጋ ላይ ነው:: ለህይወቱ ያሰጋዋል:: ፍርድ ቤቱ በእሱ ትዕዛዝና ቁጥጥር ወደ ማረሚያ ቤቱ ያስገባቸውን ተከሳሾች ሰብዓዊ አያያዝና ደህንነት የመከታተል ሀላፊነት አለበት:: የማረሚያ ቤቱ ተወካይ አሁን ያቀረበው ሪፖርት ሐሰት ነው ለማለት እጃቸውን አወጡ:: ዳኛ አዲል ግን እጃችሁን ሰብስቡ አይሆንም አለን:: የሙሉነህን ሁኔታ እናስረዳ አሁን የተባለው የሐሰት ቃል ነው ብንልም እናንተ እንድትናገሩ እድል አልሰጣችሁም አለን:: ተጨማሪ እጆች ወጥተውም ባለፈው ትዕዛዝ ያልተሰጠባቸው ጥያቄዎች አሉን አሉ:: አቤቱታ ከሆነ በመጨረሻ አለ ዳኛው::

ሚያዝያ 24/99 በዋለው ችሎትም አቤቱታ በመጨረሻ ብሎን በመጨረሻ ግን እኛ ቆመን እየተናገርን ነው ጥለውን የሄዱት:: እባካችሁ፣ ስለፍትሕ ስትሉ፣ አቤቱታችንን አንዴ አድምጡንና መልስ ስጡን አልን:: ዳኞቹም ማናቸውንም ጥያቄና አቤቱታ በመጨረሻ ታቀርባላችሁ አሁን ችሎቱ ይቀጥላል ተቀመጡ አሉን። አምነናቸው ተቀመጥን:: በመጨረሻ ግን ቪዲዮዎቹ ተሟልተው ይታዩ ብለው ለሰኔ 4/99 (ከላይ የተቀጠረበትን ምክንያቶች ማለት ነው) ዘርዝረው ትዕዛዝ ሰጥተው ተነሱ። አቤቱታ አለን ትዕዛዝ ያልተሰጠባቸው ጉዳዮች አሉ፤ ሙሉነህ በአደጋ ላይ ነው፤ የሚሉትን ቆመን ብንናገርም፣

አሁን አንሰማም፣ ሌላ ጊዜ፤ ብለውን ሄዱ:: በመጨረሻ እንሰማችኋለን ካሉን በኋላ ሲጨርሱ ተራ የማታለል የዱርዬ ሥራ ሠርተውን ሄዱ::

በግንቦት 24 እና በሰኔ 4 መካከል የቅንጅት ሊቀመንበር ዓይናቸውን ኦኘራሲዮን አድርገው ሆስፒታል በተኙበት ዕለት ማክሰኞ ግንቦት 28 ተወያዩ አሉን። ሊቀመንበሩ በእጃቸው ብዙ ማስረጃ ስላለና ለክርክሩም ወሳኝ ድርሻም ስለሚጫወቱ ከሆስፒታል ሲወጡ ብንገናኝ ይሻላል የሚል ጥያቄ አቀረብን:: ግንቦት 30 ሐሙስ ጠዋት መጥተው፣ ፍርድ ቤቱ ኢንጅኔር ሀይሉ ኖሩም አልኖሩም ለውጥ አያመጣም፤ ከፈለጋችሁ ተወያዩ እምቢ ካላችሁ ድጋሚ ዕድሉን አታገኙም ብሎ ትዕዛዝ ስለሰጠና፣ መወያየት የምትችሉት ዛሬ ብቻ ነው ስለተባልን ኢንጅኔር ሀይሉ በሌሉበት ተገናኘን:: ስንገናኝ ግን ፍርድ ቤት በማስረጃነት ከቀረቡት ቪድዮዎች ሁለቱ ማረሚያ ቤቱ አልተላከልኝም ብሎ ስላላሳየን ምን እንደሚሉ ለማወቅ አልቻልንም:: የቪዲዮና የኦድዮ ማስረጃዎች ጭብጥ ስላልተሰጠን አቃቤ ሕግ ከኛ ምን እንደሚፈልግ አላወቅንም:: ኢንጅኔር ሀይሉ እጅ ስላሉት ማስረጃዎች ጭብጥ፣ ስላላገኘናቸው አልተወያየንባቸውም:: የምስክሮች ቃል ስላልተሰጠን ለመነጋገርና የተሟላ የመከላከያ ማስረጃ ለማቅረብ መወያየት አልቻልንም:: ከቤታችንና ከማረሚያ ቤት በየጊዜው የተወሰዱብን ሰነዶችና ማስረጃዎች ስላልተመለሱልን በጣም ተቸገርን::

ከምንም በላይ ፍርድ ቤቱ ምንም ይሆን ምን አኛን ለመስማት አቤቱታ ለማዳመጥ አቃቤ ህግና ማረሚያ ቤቱ፣ ለሚያቀርቡብን ክስ መልስ ለመስጠት እንዳንነጋገር መከልከሉ፣ የእኛን በደልና ለመከላከል በሚያስፈልጉን ለፍርድ ቤቱ አቅርበናቸው ፍርድ ቤቱ ዝም ብሎ አውቆ ባለፋቸው ጉዳዮች ትዕዛዝ እንዲሰጥባቸው በተለያዩ ጊዜ ጠይቀን፣ ፍርድ ቤቱ ሊያናግረን አልቻለም:: በመጨረሻም እሰጣለሁ እያለ በመጨረሻ ጥለውን ይወጣሉ:: እንኳንስ ለመከላከል ጥያቄ ልናቀርብ እንኳ፣ ተቸገርን የመደመጥ መብት አይደለም፡ እንደሰው እንኳ መታየት አልቻልንም::

ሰኔ 4 ቀን 1999 ዓም እነዚህን ብሶታችንንና ፍርድ ቤቱ ዛሬ ነገ እያለ ትዕዛዝ ሳይሰጥባቸው ለቆየ አቤቱታዎች መልስ እንዲሰጠን ለመጠየቅ፣ ችሎቱ ሲሰየም ቆምን ለምን ቆማችሁ ብሎ ሳይጠይቀን ዝም ብሎ ቀጠለ:: እኛ አቤቱታ አለን አልን:: ዳኛው ዝም በሉ አለንና የማረሚያ ቤቱን ተወካይ ቪድዮዎች ታይተዋል ብሎ ጠየቀ:: ተወካዩም ከፍርድ ቤቱ የተላኩልንን ቪድዮዎችና ኦድዮዎች አሟልተን አሳይተናል ብሎ ዋሸ:: እውነቱ ግን ለማረሚያ ቤቱ የደረሱት ያሳየን ብቻ ሊሆን ይችላል:: ለእኛ ግን

በፍርድ ቤት ማስረጃ ሆነው ቀርበው ተከላከሉ የተባልንባቸው ሁለት ቪዲዮዎች አልታዩም:: በጣም የሚገርመው ጉዳይ ግን ቪዲዮዎች ተሚልተው አለመታየታቸውን ግንቦት 30 ቀን ለፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማመልከቻ ያስገባነውን ማረሚያ ቤቱ ለፍ/ቤቱ አልልክም ብሎ አስቀርቶት፣ ለፍርድ ቤቱ ሰኔ 4 መልስ ሲሰጥ ግን፣ እኔ በእጄ ያለውን አሳይቻለሁ እነሱ ግን ሁለት ቪዲዮ ይቀራል ብለዋል አላለም:: ሰለማመልከቻውም አላነሳም:: እኛም ይፈቀድልንና ከመሃላችን አንድ ሰው ያስረዳ። ቪዲዮዎች ተሚልተው አልታዩም:: ከዚህ በፊት ከሚያዝያ 1/99 ጀምሮ ለምናቀርባቸው ጥያቄዎች ትዕዛዝ አልተሰጠባቸውም። ፍ/ቤቱ በተደጋጋሚ ጊዜ ሊያደምጠን አልፈለገም። ዛሬ አቤቱታዎችንን ያድምጠን። ጥቂት ጊዜ ይሰጠንና ከመካከላችን አንድ ሰው ያቅርብልን አልን:: ፍርድ ቤቱ ዝም ብሎ ተቆጣ:: እንዳውም የቀኝ ዳኛውና የመሐል ዳኛው እየተቀባበሉ ማስፈራራት ያዙ:: እኛም እንደቆምን የተከበረው ፍርድ ቤት አቤቱታ አለን ማለታችንን ቀጠልንበት። ስለህግ ስለፍትሕ ለጥቂት ጊዜ እባካችሁ አድምጡን አልን:: በመጨረሻም ከ10 ደቂቃ በኋላ እንመለሳለን ብለው ወደ ወስጥ ገቡ::

10 ደቂቃ ያሉት 2 ሰዓት ከ 30 ቆይተው መጡና ውሳኔ እንሰጣለን አሉ:: ተከላከሉ ብለናችሁ ስላልተከላከላችሁ ሁላችሁም የዕድሜ ልክ እሥራትና ሞት በሚያስቀጣ ተደራራቢ አንቀፆች ጥፋተኞች ናችሁ አሉን::

በዕለቱ ለመከላከል ወስነው ጠበቃ ያቆሙና የማስረጃ ዝርዝር በጠበቃቸው በከል ይዘው የቀረቡ ተከሳሾች ነበሩ:: የጋዜጣ አሳታሚ 3 ድርጅቶችም ሰኔ 1 ቀን ለፍርድ ቤቱ አስቀድመው ማመልከቻ አስገብተዋል:: በዋስ ሆኖ የሚከላከል አንድ ተከሳሽም እንደዚሁ:: ፍርድ ቤቱ ይህ ሁሉ እየተነገረው እኛም ገና አንከላከልም ሳንል፣ ለምንድን ነው የመከላከያ ዝርዝር አቅርቡ ብዬ የሰጠኋችሁን ትዕዛዝ ያላከበራችሁት ብሎ ሳይጠይቅ፣ እኛም 2 የቪዲዮ ማስረጃ ማየት ይቀረናል እያልን፣ የራሱ ትዕዛዝ መፈፀሙን እንኳ ሳያረጋግጥ የምንከላከል መሆን አለመሆኑን እንኳ ሳይጠይቅ ለሰኔ 4 ቀጠሮ የያዙበትን ጉዳይ ሁሉ ትቶ፣ እኛ አቤቱታ አለን እያልን፣ እየለመንን፣ የክርክሩ ግማሽ አካል የመከላከል ሂደት አልፎ ጥፋተኞች ናችሁ አለን:: አንድ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብት ታግዶ በአቃቤ ሕግ የውሸት ማስረጃ ብቻ ጥፋተኛ ነህ ሲባል በኢትዮጵያ መደበኛ ፍርድ ቤት ታሪክ የመጀመሪያው ነው::

የፍትህሕ ስርዐቱ ያለበትን ደረጃና ተዓማኒነቱ ለማን እንደሆነ አሁን አረጋገጠው፡፡ የነፃና ጠንካራ ፍርድ ቤት መኖር በአገራችን አስተማማኝ ሰላምና ዴሞክራሲ ለመገንባት መሠረት ነው፡፡ እንዲሁም ሕዝባችንን በእንደዚህ ዓይነት አሳፋሪ ውሳኔ፣ ከሚደርስበት በደል ይጠበቃል በሚል እምነት ነበር እኛ መስከረም 29 ቀን 1998 ጥያቄውን ፖርላማ ከመግባት ጋር አያይዘን ያቀረብነው፡፡ የዛሬው የዳኞች ውሳኔ፣ በእኛ ላይ ከሠሩት ግፍም አልፎ፣ አገራችንን እንደ አገር በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ፊት የሚያዋርድ ሥራ ነው፡፡

http://mesfinwoldemariam.org